# የቅንጅትን ህልውና መጠበቁ ቀዳሚ ይሁን

አምባቸው ሰዋስው

የቅንጅትን ህልውና መጠበቁ ቀዳሚ ስራችን ወይም ስምሪታችን ይሁን ስል አንዳንዶች ምናልባትም የአንድን ድርጅት ጎራ የመረጥኩ ሊመስላቸው ይችል ይሆናል። ይህ አለመሆኑን ከዚህ ለጥቆ የማሳይ ቢሆንም የሕዝብን የትግል ቁጣ ከመቀ እሳተ ገሞራ ያፈነዳው ቅንጅት ላይ የክፍፍል ፃረሞታቸውን ጥላ ሲጥሉበት እሰይ ያሉና ጮቤ የረገጡ መኖራቸውን በቀጥታ የታዘብኩ ነኝና ይህን መቃወምና ቀናውን መንገድ መጠቆም ሀላፊነቴ ሆኖብኛል። ባለፈው ፅሁፌ የተነሳ የጠብቅኋቸው ጎጦች ኡኡ ብለውብኝ አውግዘውኛል። ወዳጅ ቢያወግዘኝ እንጂ ሌላውማ ቢጮህብኝ የማልሰማ ነኝና አላሰጨነቀኝም። ዛሬ ደግሞ ለምን የቅንጅት ህልውና መጠበቁ ወሳኝና ቀዳሚ ነው ስል የዚህ ስብስብ ጠላቶች ቢወርደቡኝ አይገርመኝም።

በቅድሚያ ግን ስለ ህብረትና መቀናጀት ያለኝን አቅዋም መግለፅ እወዳለሁ። ተባበሩ ወይ ተሰባባሩ ሲሉ የነበሩት እነ ዶክተር መራራ ዛሬ ከወያኔ እንጂ ከሕዝብ ሲተባበሩ የሚታዩ አይደሉምና በበኩሌ ይህን ንግግር ሕዝብ አሰማ የሚለውን አልቀበለውም። ሁሉ ድርጅት መተባበር አለበት በሚልም አላምንም። ክብደት ያላቸውና በኢትዮጵያዊነታቸው ላይ ምንም ጥርጥር የማይነሳባቸው ድርጅቶች ነው መተባበር ያለባቸው። እውነት አውነት እላችኋለሁ በተባለው መሰረት ለመሆኑ ዛሬ ስንቱ ድርጅት ነኝ ባይ ነው በቂ አባላት ያሉት? ስንቱ ነው የሚንቀሳቀሰው በሚገባ? ዜሮ ምናባቱ ባዮች የሆኑቱ የሆነ ቁጥር ፅፈው ዜሮውን ከወደኋላው በማዥጎድጎድ ይህን ያህል አባል አለን ቢሉ ማን ያምናል? በስመ ህብረትስ ከነፍሰ ገዳዮች ጋር መተባበሩ ያዋጣል? ለነዚህ ሁሉ ዋና ጥያቄዎች ገና ግልፅ መልስ አልተሰጠም። ይህ በዚሁ ይቆይና በበኩሌ ቅንጅትን መንከባከቡ ቀዳሚ ነው ስንል በቂ ምክንያቶች አሉኝ። ይህን ታሪካዊ ስብስብ ለማጥፋት ልዩ ልዩ ሀይሎች ተቀናጅተውና ተባብረው መሰማራታቸው ይታወቃል። ይዘርዘሩ ከተባሉ የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፤

- የአሜሪካ አስተዳደር
- ወያኔ
- የዶክተር ብርሀኑና አንዳርጋቸው ፅጌ አንጃ
- ይህን አንጃ የሚደግፉት ሌሎች አንጃዎች

ቅንጅት ሲቀናጅ በሁሉም መስክ በተጠና መልኩ ተካሂዷል ማለት አይቻልም። ብዙ ተከታይና አባላት የነበረው መኢአድ ደካማ ከነበሩት ከቀስተዳመናዎችና ሰልፉ ግልፅ ካልነበረው ከልደቱ--ኢዴፓ ጋር መቀናጀቱ ብልህነት ነበር ወይ ለሚለው የሚሰጠው መልስ አዎንታዊ ነው ማለት አይቻልም። አቀነጃጀቱ ችግር ቢኖረውም ቅንጅት በትግሉ መድረክ ለሕዝብ ተስፋ በመስጠቱ ያን ያህል ሱናሚ የሆነ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አማክሎ እውነትም የትግል መንፈስ በመሆን ታሪክን ፅፏል። መንፈስ በመባሉ ብዙዎች የሽሙጥ ትችት ቢያሰሙም በእኔ አስተያየት ቅንጅት በእርግጥም መንፈስ ነበር። ከሆነ ድርጅት የተወሰነ ዓላማና ግብ ባሻገርና በበለጠ የሕዝብን የትግል ግብ ያቀፈና ያንፀባረቀ ነበር። በቅንጅት አማካይነት ሁሉም ተቃዋሚ ድርጅት ማለትም የኢትዮጵያን አንድነት የተቀበለው ሁሉ ተወክሏል፤ተንፀባርቋል። ቅንጅት ፀረ ወያኔ ለውጥን ያስተጋባ ነበረና ይህ ደግሞ የሁላችን ጩኸት ነው። ቅንጅት ኢትዮጵያዊነትን ያከበር ነውና ይህ ደግሞ የብዙዎቻችን አቅዋም ነው። በቅንጅት ውስጥ ሁላችንም ተወክልናል ለማለት የደፈርኩት በዚህ እንጂ እነ አያ ብርሀኑና ልደቱ ወይም ቀልደኛው ደበበ እሸቱ ወክለውናል ብዬ ለመቃዠት አይደለም።

ቅንጅት ዛሬ በከፋፋዮች ሴራ ችግር ገጥሞታል። በወሳኝ የትግል ጊዜ እነ ልደቱ ከድተውታል። በህብረቱ በኩል ደግሞ እነ በየነና መረራ መክዳታቸው የቅንጅትንም ትግል ጎድቷል። በነገራችን ላይ በየነ ጴጥሮስ የወያኔ ሚኒስቴር ሆኖ ሰርቶ እያለ እንዴት ኢሕአፓና ሌሎችም የህብረት ጓደኞቻቸው እንዳደረጉት ገና መጠየቅና መመለስ ያለበት ነው። ቅንጅትን እነ ብርሀኑ የከዱትም ከቃሊቲ በፊት ነው። ክቡር ኢንጂኔር ኃይሉ ሻውል በዚህ ተወቀሱ በዚያ የሕዝብን ድምፅ አድምጠው በወያኔ ፓርላማ አልገባም ብለው ፀንተው በመቆየታቸውና አመራር በመስጠታቸው የሕዝብን ከበሬታ ከማግኘታቸው ሌላ የጠላትን የከፋ ጥላቻ አትርፈዋል። በእሳቸው ላይ እነ ኤልያስ ክፍሌና ሌሎች እያዘነቡ ያሉት ፀያፍ ቸነፈር ሲመረመር እሳቸው እየሰሩ ያሉት አስመስጋኝ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። ወራዳው ኤልያስ ክፍሌ በእሳቸው ላይ የከፈተው ዘመቻ ውድቅ ሆኖበታል። የእነ ብርሃኑና ብርቱካን ወይም የደበበ እሸቱ (ቂቂቂ አስቂኝ ፖለቲካ!!!) አንጃነት ደግሞ የቅንጅትን ምሳሌነት የሚበርዝ አይደለም። ቅንጅትን በተመለከተ ወያኔ የበኩሉን ጥቃት ለማድረስ የጣቱን መታወቂያ ለልደቱ ስሙን ደግሞ ለተለጣፊ ሰጥቷል። ቅንጅት ስሙን ይዞ ቀጠለ አልቀጠለ የተነሳበት ዓላማና መንፈሱ ለሀገር ጠቃሚና አሰባሳቢ በመሆኑ በቀዳሚ ደረጃ ለህልውናው መታጋላችን አስፈላጊ ነው። ቅንጅት ስንል ብርሀኑ ወይም አንዳርጋቸው ማለት ሳይሆን የሕዝብን የትግል መንፈስ የሚያንፀባርቅ በመሆኑ ለህልውናው መጠበቅ በቀዳሚነት መታገላችን አስፈላጊ ነው። ቅንጅት ስንል የሆነ አንድ ድርጅት ሳይሆን የሕዝብንና የተቃዋሚዎችን ሁሉ አጀንዳ ማለታችን ነው። ቅንጅት ስሙ ተቀማ አልተቀማ በተከበሩ ኢንጂኔር ኃይሉ የሚወከለው አቅዋም ግን የሕዝብ ነውና ሙሉ ድጋፍን ሊሰጠው ይገባል። በቅንጅት አንጃዎች ና ደጋፊዎቻቸው የተጀመረው ዘመቻ መክሸፍ መሸነፍ አለበት። ቅንጅትን ስንደግፍ የምንደግፈው ኢትዮጵያዊነትን ነው። ሀገር ወዳድነትን ነው። ዴሞክራሲያውነትነን ነው። የሀገር አንድነትን

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ነው። ዜጎችና ሀገር ወዳድ ድርጅቶች ሁሉ ከዚህ የተለየ ዓላማ የላቸውም። ቅንጅት የሕዝብን ትኩረት ስቧል። ለውጥ ፈላጊው ሁሉ የደገፈው በውሱን ድርጅታዊ ቀመር ሳይሆን በሀገራዊ አቅዋም ነው። የቅንጅትን ህልውና መደገፍ ማለትም ስሙን ጠበቀ አልጠበቀ ይህን ሀገራዊ ፍላጎት ማስቀደም ማለት ነው። ለዚህም ነው የቅንጅትን ህልውና መጠበቅ አለብን የምለው። ቅንጅት አንድ ድርጅት ሳይሆን ሀሉም ሀገር ወዳድ ድርጅት ነው። ኢንጂኔር ኃይሉ አንድ እንግሌ ሳይሆኑ የኢትዮጵያን ሕዝብ ዋና ፍላጎት አንፀባራቂ ናቸው። ወላዋይና ከሀዲ እንበል ከተባለ ደግሞ ብርሀኑ ሆነ አንዳርጋቸው፤ወዲ በጋሻውም ሆነ ፈቃደ ሸዋቀና፤ ከሀዲ ልደቱም ሆነ ጸንጤ ብርቱካን ሁሉም የቅንጅትን መሰረት የሚንዱ አይደሉም። ስየ አብረሃ አልን ሌላ የቆሸሸው ሁሉ በተዓምር ሕዝባዊ አይሆንም። ቅንጅት ስንል የፀዳ ሕዝባዊነት ማለት ነው። ክቡር ኢንጂኔር ኃይሉ የቅንጅት መሪ ናቸው። የቅንጅት አንጻ ሆነ የኢሕአፓ አንጻ የታሪክ አተላዎች ናቸው።

ለምን ቅንጅትን መደገፍ አለብን? ቅንጅት በሕዝብ በመደገፉ። ቅንጅት የሕዝብን ፍላጎት በማቀፉ። ቅንጅት ስሙን ጠበቀ አልጠበቀ የአያሌ ተቃዋሚ ድርጅቶችን አቅዋሞች በማንፀባረቁ። ሕዝባዊ በመሆኑ። ቅንጅት የሕዝብን ልብን በመማረኩ። ቅንጅት ስሙን ሊያቆሽሹት ከተነሱት የተለየ በመሆኑ። በአሁኑ ጊዜ ቅንጅትን ስሙንም መለያውንም ቀምተውታል ግን ማንነቱን ማንም አልቀማውም። ለዚህም ነው ይህን ሕዝባዊ ድርጅት መደገፉ ቀዳሚ መሆን የሚገባው። ዛሬ በኢንጂኔር ኃይሉ ሻውል የሚመራውን ቅንጅት መደገፍ አለመደገፍ ወሳኝ ጥያቄ ነው። የቅንጅት አንጻዎች የወያኔ ተለጣፊዎች ናቸው። የሁሉም አንጻ ያው ተለጣፊ ነው። ፀረ ወያኔ ድርጅቶችን የሚቃወም ጤነኛ ነው ሊባል አይችልም። ቅንጅትን ለምን መደገፍ አለብን? የሀገርንና የሕዝብን ተስፋ ይወክላልና። የሁላችንንም የልብ ትርታ ያዳምጣልና። ሀገራዊ ነውና። ሌላ የሚባል የለም። ለቅንጅት ህልውና በመቆም ሁላችንም ለኢትዮጵያ ደህንነት እንቆማለን።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com